የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፷፱
አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 69
ADDIS ABABA, this January 25th, 2020

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፷፱/፪ሺ፲፪**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማሻሻያ አዋጅ**

**ገፅ------------------------------ ሺ፮፻፵፱**

**CONTENT**

**The Amendment of the Addis Ababa City Government Office of the Auditor General Proclamation**

**Page --------------------------- 1649**

**አዋጅ ቁጥር ፷፱/፪ሺ፲፪**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፲ ማሻሻያ አዋጅ**

የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በከተማው የሚገኙ የመንግስት አካላት ማለትም የህግ አውጪውን፣ የፍትህና አስፈጻሚ አካላት ላይ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚደረገው ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረው ሚና የጎላ በመሆኑ የተቋሙን ሙያዊ ነጻነት ማስጠበቅ ውስጣዊ አደረጃጀቱን ማሻሻል፣ ማዘመንና ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**PROCLAMATION NO. 69/2020**

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT OFFICE OF THE AUDITOR GENERAL RE-ESTABLISHMENT PROCLAMATION NO. 29/2012**

**WHEREAS,** it has been found necessary to ensure the professional freedom, improve, modernize and strengthen the internal organization of the institution as the Addis Ababa City Office of the Auditor General has a paramount significance in the comprehensive activities which are carried out so as to ensure transparency and accountability within the legislative, judicial and executive organs of the City Government;

የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ባለሙያዎች ነጻነታቸው ተጠብቆ፣ መብትና ግዴታቸውን በውል ለይተው በማወቅ ተግባርና ሀላፊነታቸውን ግልጸኝነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ መወጣት እንዲችሉ ለማድረግ፤

የኦዲት ስራውን ወቅታዊና ፈጥኖ ማስተካከያ እርምጃ ከመውሰድ አንጻር እየታየ ያለውን የመንግስት የሀብት ብክነት መልክ ለማስያዝ የሚያስችል ተደራሽ አደረጃጀትና አሰራር በመዘርጋት ኃላፊነቱን መወጣት እንዲችል ለማድረግ አሁን በስራ ላይ ያለው የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፲፪ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሸሻለ) አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) መሠረት የከተማው ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ " የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፷፱/፪ሺ፲፪ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፲፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

**WHEREAS,** so as to enable professionals of the Office of the Auditor General to precisely understand their rights and obligations and carry out their duties and responsibilities in a transparent and accountable manner through maintaining their freedom;

**WHEREAS,** it has been found necessary to amend the existing establishment proclamation No. 29/2012 of the Office of the Auditor General so as to enable it to carry out its responsibilities through establishing accessible organizational structure and procedures that enable it to rectify the problems exhibited in making the auditing activities up-to-date and in taking corrective measures promptly which in turn leads to the resource wastage of the government;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub-Article (1) (a) of Article 14 of the Revised Charter of the Addis Ababa City Government Proclamation No. 361/2003 (as amended); the Addis Ababa City Council has issued this Proclamation as follows.

**1.<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as: "The Addis Ababa City Government Office of the Auditor General Re-establishment Proclamation (Amendment) Proclamation No.69/2020."

**2. <u>Amendment</u>**

The Addis Abeba City Government Office of the Auditor General re-establishment Proclamation No. 29/2012 is amended as follows:

፩) ከአዋጁ አንቀጽ ፬ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፭ ተጨምሯል፡-

“፭ <u>ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ስለማቋቋም</u>

፩. መስሪያ ቤቱ የኦዲት ሽፋኑን ለማሳደግ እንደ አሰፈላጊነቱ በከተማው ውስጥ ቅርንጫፍ ሊያቋቁም ይችላል፤

፪. የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሙያን መሰረት አድርጎ በዋና ኦዲተሩ ይመደባል፤

፫. የቅርንጫፉ ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለመስሪያ ቤቱ ይሆናል፡፡”

፪) ከአዋጁ አንቀጽ ፭ በኋላ ያሉ አንቀጾች እንደቅደመ ተከተላቸው ተሸጋሽጓል፤

፫) የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (እንደተሻሻለ) ንዑስ አንቀጽ /፮/ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

“፮. የመስሪያ ቤቱን መዋቅር፣ የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማ ጥቅም ክፍያ በማጥናት ለከተማው ካቤኔ ያቀርባል፤ በካቢኔው ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡”፤

፬) ከአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (እንደተሻሻለ) ከንዑስ አንቀጽ ፰ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፱ ተጨምሯል፡፡

“፱. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ውስጥ የተቀመጡት መሠረታዊ ዓላማዎችና መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሠረት የመስሪያ ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፡፡”

**1)** The following new Article 5 is added following Article 4 of the Proclamation:

**“5**. **<u>Establishing Branch Offices</u>**

1) The Office may, as it is found necessary, establish branches in the City so as to improve the audit coverage;
2) The head of the branch office shall be assigned by the Auditor General based on profession;
3) The branch Office shall be accountable to the Office.”

**2)** Articles following Article 5 of the Proclamation are re-arranged in their order respectively.

**3)** Sub-Article (6) of Article 14 (as amended) of the Proclamation is amended as follows:

“6. study the structural organization, salary scale and benefit payments of the Office and submit same to the Cabinet of the City; implement the thereof upon its approval by the Cabinet.”

**4)** The following new Sub-Article (9) is added following Sub-Article (8) of Article 14 (as amended) of the Proclamation:

“9. without prejudice to the stated objectives and principles in the Civil Servants' Proclamation of the Addis Ababa City Government, hire, administer and dismiss employees of the Office according to a Regulation to be issued by the Cabinet.”

## ፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ (ኢ/ር)

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

## 3. <u>Effective Date</u>

**This Proclamation shall come into force as of 25th day of January, 2020.**

**Done at Addis Ababa, this 25th day of January, 2020**

**Takele Umma Banti (Eng.)**
**Deputy Mayor of Addis Ababa City**